የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፫ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No. 31
ADDIS ABABA 31st May, 2012

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፯፻፴፰ /፪ሺ፬ ዓ.ም

የ፪ሺ፬ በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት ተጨማሪ በጀት አዋጅ …... **ገጽ ፮ሺ፫፻፴፬**

**<u>CONTENTS</u>**

**Proclamation No.738/2012**

2004 E.C. Fiscal Year Federal Government Supplementary Budget Proclamation. ... Page 6334

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፴፰ /፪ሺ፬ ዓ.ም

## <u>የፌዴራል መንግሥት ተጨማሪ በጀት አዋጅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፩) እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰/፪ሺ፩ አንቀጽ ፳፯ መሠረት ለተጨማሪ ለካፒታል ሥራዎች የሚከተለው ታውጇል።

<u>አንቀጽ ፩</u> ይህ አዋጅ "የ፪ሺ፬ በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት ተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር ፯፻፴፰ /፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

<u>አንቀጽ ፪</u> ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፫ ጀምሮ ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፬ በሚፈጸመው በአንድ የበጀት አመት ጊዜ ውስጥ በፌዴራል መንግሥት ከሚገኘው ገቢ ላይ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ውስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሎ እንደተመለከተው፦

## PROCLAMATION No. 738/2012

## <u>FEDERAL GOVERNMENT SUPPLEMENTARY BUDGET PROCLAMATION</u>

In accordance with Article 55(1) and (11) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and in accordance with Article 27 of the Federal Government Financial Administration Proclamation No. 648/2009 a supplementary of capital budget is hereby proclaimed.

Article 1 This Proclamation may be cited as the "2004 E.C Fiscal Year Federal Government Supplementary Budget Proclamation No.738/2012".

Article 2 There is hereby appropriated a Supplementary Budget to the Federal Government, for the Fiscal Year commencing on Hamle 1, 2003 E.C. and ending on Sene 30, 2004 E.C. from Federal Government Domestic revenue:

ለካፒታል ወጪዎች ብር ፬ ቢሊዮን

/አራት ቢሊዮን ብር/ በተጨማሪ ወጪ ሆኖ በፌዴራሉ መንግሥት እንዲከፈል በዚህ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ተፈቅዷል፡፡

አንቀጽ ፫ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ለየመሥሪያ ቤቶቻቸው ሥራና አገልግሎት ከፌዴራል መንግሥት ገቢ በዚህ አዋጅ ለተጨማሪ ሥራዎች የተፈቀደላቸውን ተጨማሪ በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ እንዲከፍል ተፈቅዶለት ታዟል፡፡

አንቀጽ ፬ በዚህ አዋጅ የተፈቀደው የተጨማሪ በጀት በ፪ሺ፬ በጀት ዓመት የበጀት አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፱/፪ሺ፫ በተመለከተው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፳፫ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት



For Capital Expenditure Birr 4,000,000,000

/Four Billion Birr/ as set forth in the schedule attached hereto.

Article 3 The Minister of Finance and Economic Development is hereby authorized and directed upon the request of the heads of the concerned government organs, to disburse out of the Federal Government revenues the additional amount appropriated herein for the undertakings of their respective organs.

Article 4 Utilization of the Supplementary Budget shall be made in accordance with the Budget Proclamation No. 719/2011.

**Done at Addis Ababa, this 31st day of May, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**